## የትምህርት አመቱ ካለቀ በኋላ ምን ማድረግ እንዳለብዎት

የትምህርት አመቱ ካለቀ በኋላ የኦርካ ካርድዎ አሁንም ጠቃሚ ነው!

### ማወቅ ያለብዎት ነገር ይኸውና፡-

**ካርድዎን ያስቀምጡ፡-** ካርድዎ እስከ ኦገስት 31 ቀን 2026 ድረስ ይሰራል።

**ጊዜው ካለፈ በኋላ ገንዘብ ይጫኑበት፡-** ከኦገስት 2026 በኋላ፣ ካርድዎን መጠቀምዎን መቀጠል ይችላሉ፣ ነገር ግን የራስዎን ገንዘብ መጨመር ያስፈልግዎታል። ይህንን በኪንግ ካውንቲ የደምበኛ አገልግሎት ቢሮ ወይም በኢንተርኔት በ MyORCA.com ላይ ማድረግ ይችላሉ።

**ብቁ ከሆኑ፣ አዲስ ካርድ ይውሰዱ፡-** ልጅዎ በሁለቱም ማለት 2024-2025 እና 2025-2026 የትምህርት ዓመታት በሲያትል መዋለ ሕጻናት ፕሮግራም (SPP) ከተመዘገበ/ች፣ ወዲያውኑ አዲስ የኦርካ ካርድ እንልክልዎታለን።

የካርድዎ ቀን ካለቀ በኋላ ለትራንዚት ለመክፈል ስጋት ካለዎት፣ በኪንግ ካውንቲ ሜትሮ ድህረ ገጽ ላይ የቅናሽ ዋጋ አማራጮችን ይመልከቱ፡- kingcounty.gov/WhichORCAFare። የቤተሰብዎን የመጓጓዣ ፍላጎቶች ለመደገፍ እኛ እዚህ አለን!

## ካርዴ ጠፋብኝ። ምን ላድርግ?

ካርድዎ ከጠፋብዎ አይጨነቁ! ምትክ ካርድ ለመጠየቅ፣ የሚከተሉትን ማድረግ ይችላሉ፡-

- በ DOT_TAP@seattle.gov ላይ ኢሜል ይላኩልን ወይም
- በ 206-256-6722 ይደውሉ ወይም ቴክስት ይላኩልን።

በቀላሉ አዲሱን ካርድዎን የምንልክበትን ስምዎን እና የፖስታ አድራሻዎን ይንገሩን።

**ጠቃሚ፡-** ምትክ ከጠየቁ በኋላ የድሮ ካርድዎን ካገኙት እሱን መጠቀም አይችሉም።

8.2025

# የመዋለ ሕጻናት መጓጓዣ ድጋፍ ፕሮግራም

(PRESCHOOL TRANSIT SUPPORT PROGRAM)





AMHARIC

Seattle Department of Transportation

## የመዋለ ሕጻናት የትራንዚት ድጋፍ ፕሮግራም ምንድን

የሲያትል ትራንስፖርት መምሪያ (SDOT) ልጅዎን መዋለ ሕጻናት ማድረስ ከባድ ሊሆን እንደሚችል ያውቃል! ለእርስዎ ቀላል እንዲሆንልዎ ለማድረግ፣ ለሁሉም ገቢያቸው ብቁ ለሆኑ ቤተሰቦች ነጻ፣ ያልተገደበ መጠቀሚያ ኦርካ (ORCA) ካርድ በዚህ የትምህርት ዘመን ለመጠቀም በፖስታ እየላክን ነው። ይህ ካርድ የመዋለ ሕጻናት ተማሪዎን ወደ ትምህርት ቤት ለማድረስ እና ለመመለስ ይረዳዎታል ብለን ተስፋ እናደርጋለን። የኦርካ ካርድ ጥቅማ ጥቅም የሚከፈለው በሲያትል ትራንዚት ተነሳሽነት (ደንብ) (Seattle Transit Measure) ሲሆን ይህም ለስድስት አመት፡ በመራጮች የጸደቀ የሽያጭ ታክስ ነው።

## እንዴት እንደሚሰራ እነሆ!

### የሚከተሉትን ማድረግ ይችላሉ፡-

- ምንም እንኳን ከአንድ በላይ የመዋለ ሕጻናት ተማሪዎች በቤትዎ ውስጥ ቢኖሩም አንድ የኦርካ ካርድ ያግኙ።
- በሁሉም የክልል የህዝብ ማመላለሻዎች ላልተገደበ ጉዞ የኦርካ ካርድዎን በነጻ ይጠቀሙ። የኦርካ ካርድዎን እስከ ኦገስት 31፣ 2026 ድረስ ይጠቀሙበት።
- ካርድዎን በቀን 24 ሰዓት፣ በሳምንት 7 ቀናት ይጠቀሙበት።

**ያስታውሱ፡-** የመዋለ ሕጻናት ተማሪዎችዎ እና 18 እና ከዚያ በታች የሆኑ ወጣቶች መጓጓዣ/ትራንዚት ላይ በነጻ መሳፈር ይችላሉ። ለወጣቶችዎ ነፃ የኦርካ ካርድ ለማግኘት ከፈለጉ፣ FreeTransitPass.comን ይጎብኙ። እድሜያቸው ከ13-18 ለሆኑ ህጻናት የORCA ካርዶችን እንዲያገኙ እናበረታታዎታለን።

## አዲሱ የኦርካ ካርድዎን እንዴት እንደሚጠቀሙ

### አውቶብስ ላይ መሳፈር

1. አውቶቡስ ውስጥ ከገቡ በኋላ የኦርካ ካርድዎን በካርድ አንባቢው ላይ ያስነኩ።
2. ሹፌሩን ከአውቶቡስ መውረድ እንደሚፈልጉ ለማሳወቅ በመውረጃ ፊርማታዎ ከመድረስዎ በፊት ቢጫውን ገመድ ሳብ ያድርጉት።

### ስትሪትካር ላይ መሳፈር

1. ከመሳፈርዎ በፊት የኦርካ ካርድዎን በስትሪትካር ፕላትፎርም ላይ ያስነኩ።
2. መውረድ እንደሚፈልጉ ለአሽከርካሪው ለማሳወቅ የማቆሚያ መጠየቂያውን ይጫኑ።

### ቀላል ባቡር ላይ መሳፈር

ባቡሩ ውስጥ ከመግባትዎ በፊት የኦርካ ካርድዎን ፕላትፎርሙ ላይ ያስነኩ።

## የኦርካ ካርዴን የት መጠቀም እችላለሁ?

ካርድዎን በሚከተሉት መጓጓዣዎች ላይ ከፍለው ለመጓዝ መጠቀም ይችላሉ፡-

- የኪንግ ካውንቲ ሜትሮ አውቶቡሶች - አክሴስ እና የሜትሮ ፍሌክስ አገልግሎቶችን ጨምሮ
- የኪንግ ካውንቲ የውሃ ታክሲ
- ሲያትል ስትሪትካር (Seattle Streetcar)
- የሲያትል ሴንተር ሞኖሬል
- የሳውንድ ትራንዚት (ቀላል ባቡር፣ ባቡሮች፣ እና አውቶቡሶች)
- ኮምዩኒቲ ትራንዚት
- ፒርስ ትራንዚት
- ኪትሳፕ ትራንዚት (አውቶቡሶች እና ፈጣን ፌሪ)
- ኤቨሬት ትራንዚት

### ትራንዚት ለመጠቀም እነዚህን አጋዥ ግብአቶች ይመልከቱ!

**One Bus Away (ዋን ባስ አዌይ)፡-** ለአውቶቡሶች እና ለቀላል ባቡር የእውነተኛ መድረሻ ጊዜ መረጃን ለማግኘት ይህንን መተግበሪያ ያውርዱ።

**Google Maps (ጉግል ማፕስ)፡-** የትራንዚት አቅጣጫዎችን እና የአሁናዊ መድረሻ ሰዓት መረጃዎችን ለማግኘት ጉግል ካርታዎችን በኮምፒውተር ወይም በስልክ መተግበሪያ ይጠቀሙ።

**King County Trip Planner (የኪንግ ካውንቲ የጉዞ ዕቅድ አውጪ)፡-** ለጉዞዎ የመጓጓዣ አቅጣጫዎችን ለማግኘት ይህንን ድህረ-ገጽ ይጠቀሙ፡- tripplanner.kingcounty.gov/

